# " ጦሰኛው መለስ! "

የጐንቻው!

ውል አዳሩን ሞተ በቁሙ መለስ፤
'የሃጢያን ቀጠሮ' ቁርጡ ቀን ሲደርስ፤
በእልፍኝ ተጨርሶ ውጭ ሊፈወስ፤
በድኑን ተጠረዘ ነፍስ-አልባው ንጉስ፤
ጓዳ እንዳይሰነፍጥ 'ሊታረስ በነርስ'፤
''ሞቱን ሲገላገል እጁን ሲንተራስ፤
'ሩሕያ ሲያል' እርቃን ብራስልስ፤
ሚስት፤ልጅ፤ታጋዮቹ ተሻሙ በውርስ፤
**ከሞቱ አሟሟቱ ጦሰኛው መለስ።**

መግደል አዘውትሮ ሞቱን ሊያሳልስ፤
አውሮፓ አከነፉት እንዲዘራ ነፍስ፤
በአሳር የነገሰች የወንጀል መንፈስ፤
'ነፍስ አባት' ፍለጋ ስትገሰግስ፤
ሳተናው ጦለባት የአበሻው ንፋስ፤
አየር በአየር ቀረች ሳትንከላዎስ፤
**ሲያል ይቀበላት አባ ዲያቢሎስ ።**

የሄግ ዶሴያቸውን የምድራዊ ክስ፤
በወዲያኛው ዓለም እንዲወራረስ፤
ቅረተ-አካላቸው ጠድፎ በመድረስ፤
አሻራ እንዲሰጡ 'አንደበተ-ቢስ'፤
አይነቱ እዳ ከፋይ አራሱ መለስ፤
**ገቡ በቃሬዛ ነፍስ-አልቦው ንጉስ ።**

'ፈርዖን ጣዖቱ' ምስሉ እስኪላበስ፤
ማቀዝቀዣ አኖሩት እንዳይፈራርስ፤
ሙቶም ያንቃቁታል አፈር እንዳይቀምስ፤
ሲያል አጃቢዎች ደንገጡር መንፈስ፤
'አጥም በሚያከስሉ' 'የኑዛዜ ጢስ'፤
ካመዱ እስኪቀባ አልጋ ወራሽ ጽንስ፤
የሸሙጥ መርዷቸው እረፍት 'ብራስልስ'፤
በጓዳ እያጦፉ የለቅሶ ድግስ፤
'እርም ቋንጣ' ሰቅለው ስላሴ መቅደስ፤
'ለአቡን መቅስፍት ሆነ ገል-አፈር ሲፈርስ'፤
**ከሞቱ አሟሟቱ ጦሰኛው መለስ ።**

ድብብቆሽ ሲሆን የየቀን ውሎው፤
አላበዙትም ወይ በአዘቡቱ አርፈው፤
ሲመጡም ሲሄዱ አላሉንም 'ቻው'፤
ባይሆን መንግሥትዎን ፓርላማ ቀርበው፤
እንቆቅልሽ ሆኑ መለሰ ዜናው፤
**'ጆሮ ዳባ' እያሉን 'ምድር ጥግ' ይዘው።**

መንግሥት አሸበሩ ጠፍተው አጥፍተው፤
ተናካሽ ውሾቹን በመረን ለቀው፤
ሕዝብ ያስጨርሳሉ በየአደባባው፤
አንድ ቀን ሳይሰሙን 'ሁሌ አሸልበው'
**መከራ አተረፉን ኑረውም ሄደው።**

እኒህ የኛ ንጉስ ጫካ ያፈራቸው፤
ሲከርሙም ሲሄዱ በወፍ ሚስጥራቸው፤
'አገር የሚያቀኑት' አንድ ስፍራ ናቸው፤
ኪሳራ እያጋሩን ትርፉ የግላቸው፤
ምድር የቆለሉት እዳ ከምራቸው፤
'ጉልላት' ተንዶ አፈር ተጫናቸው፤
**ምስጡ እራሳቸውን በቁሙ በላቸው።**

ሳር ቅጠል አቢሾ ቀለብ ምንዣካቸው፤
ዋሻ ያስደቆነ ቆሪጥ አምላካቸው፤
ምን ግብር ጐደለ መጣ በራሳቸው፤
ቆባቸውን ዘልቆ የመላለጣቸው፤
**'በአጥንት የገባ' ነው ደዌ በሽታቸው ።**

የተጣባ ምኙገር ከሰውነታቸው፤
'ዙፋኑ ቆርቁሮ' ስላልተመቻቸው፤
የሃያ ዓመት ቅንጦት ስለሰለቻቸው፤
ድሎትን ድል ነሱት 'ግርማዊነታቸው'
'መነው ተሰውሩ' ይህ ዓለም በቃቸው፤
በምድርም በሰማይ እንደየስራቸው፤
'ይባረኩ ንጉስ' በስተፍጻሜያቸው፤
'አረፉልን መለስ' በግራ ጐናቸው፤
የሞት ባለንጀራን ቀብረን አናምናቸው፤
'ሳጥኑ ይማገድ መስቀል ደመራቸው'፤
'እሳት ክብረት ጭረን ሙቀን አንሸኛቸው'፤
**ዘላለም 'መንገዱን ጨርቅ ያርግላቸው'።**

20.07.12

የጐንቻው! yegonchaw@yahoo.co.uk

መንገዱን ጨርቅ ያድርግልዎ !!!



